የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 27
ADDIS ABABA 14th April, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፭/፳፻፲፬

የኢትዮጵያ ደን ልማትን ሥልጣን፣ ተግባርንና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................ገጽ ፲፬ሺ፩፻፶፭

## Content

Regulation No. 505 /2022

Council of Ministers Regulation to Determine the Power, Duties and Organization of the Ethiopian Forestry Development........................Page 14155

## ደንብ ቁጥር ፭፻፭/፳፻፲፬

## የኢትዮጵያ ደን ልማትን ሥልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፳፻፲፫ አንቀጽ ፵፰(፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ ደን ልማትን ሥልጣን፣ ተግባርንና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፭/፳፻፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## REGULATION NO. 505/2022

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE POWER, DUTIES AND ORGANIZATION OF THE ETHIOPIAN FORESTRY DEVELOPMENT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 48(2) of the definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the “Regulation to Determine the Power, Duties and Organization of the Ethiopian Forestry Development, Council of Ministers Regulation No. 505 /2022”.

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ **"ደን ልማት"** ማለት ሰው ሠራሽ ደን፣ የተፈጥሮ ደን፣ የደን አያያዝና አስተዳደር፣ የደን ጥበቃ፣ የደን ሀብት መለካትና መረጃ ማደራጀት፣ ደንን መጠቀም፣ የደን ግብይት፣ የደን ኢንዱስትሪ፣ ጥምር ደን ግብርና፣ የደን ምርምር እና ሥልጠና እንዲሁም የተጎሳቆለ መሬትን በሥነ-ሕይወታዊ መንገድ እንዲያገግምና እንዲለማ ማድረግ ነው፤

፪/ **"የደን ጥበቃ"** ማለት የተፈጥሮ ደንንና ሰው ሠራሽ ደንን ከተከላ ጀምሮ ለምርትና ለአገልግሎት እንዲውል ጉዳት ከሚያደርሱ ሕገ ወጥ የደን ምንጣሮና መራቆት፣ የደን እሳት፣ ነፍሳት-ተባዮችና በሽታ፣ መጤና ተዛማች አረሞች፣ ከእንስሳት ንክኪና ሌሎች ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን መከላከልና መንከባከብ ነዉ፤

፫/ **"የደን አያያዝና አስተዳደር"** ማለት ለዘላቂ የደን ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦትና በሳይንሳዊ ዘዴ የሚካሄድ የደን እንክብካቤ፣ ሚዛናዊ የደን አጠቃቀም፣ ለደን ልማት እና ጥበቃ አስፈላጊ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ሥርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ነዉ፤

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ **"Forest Development"** means the protection, management, use and administration of natural or man made forests; forest inventory; forestry data management; value addition and marketing of forest products; forest industries; research and training on forestry and agroforestry; and restoration of degraded landscapes using biological means;

2/ **"Forest Protection"** means protecting forests from illegal deforestation and forest degradation, from forest fire, pests and diseases, invasive species, be it exotic or not, and other natural or man made damages;

3/ **"Forest Management and Administration"** means ensuring availability of inputs for forestry development, establishing, managing forests in a scientific way, ensuring balanced forest use, and putting in place and operationalize legal ,economic and social framework for sustainable forest management;

፬/ **"የደን ሀብት መለካት"** ማለት የደንና የደን መሬትን መለየት፣ መከለልና በውስጡ ያለውን ሀብት በሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም መረጃ መስብሰብና መተንተን ነው፤

፭/ **"ደንን መጠቀም"** ማለት ለደን ሀብት አጠቃቀም በወጣ ሕግ፣ ደረጃ እና መመሪያ መሠረት ምርት መሰብሰብ፣ ለፍጆታ ማዘጋጀት፣ ማጓጓዝ፣ ለገበያ ማቅረብ እና ከደን ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ነው፤

፮/ **"የደን ውጤትና ሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ግብይት"** ማለት የደን ዉጤቶችና ሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክምችት፣ ግዢ፣ ሽያጭና ማጓጓዝ ሥርዓት ነው፤

፯/ **"የደን ኢንዱስትሪ"** ማለት በደን ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ የሚያቀርቡ አምራች ተቋማት ነው፤

4/ **"Forest Resources Assessment"** means identifying, measuring, and certifying forestland and forests in a scientific way to assess changes in forest cover and value, and compile, and analyze, the information so generated;

5/ **"Forest Utilization"** means using forest resources as per forest laws, standards and management plans and includes processed of harvesting, processing, storing, transporting, and marketing of forest products and forest services;

6/ **"Marketing of Forest Products and Forest-Based Ecosystem Services"** means the system of buying, storage, sales, and transportation of forest products and forest ecosystem services;

7/ **"Forest Industries"** means forest industries engaged in the value addition and processing of forest products;

፰/ **"የደን ምርምር"** ማለት በደንና ጥምር ደን ግብርና ልማት፣ አያያዝ፣ ጥበቃና አጠቃቀም፣ በደን ሥርዓተ-ምህዳር፣ በደንና አየር ንብረት ለውጥ፣ በደን ምርት እሴት መጨመር፣ በፖሊሲና ምጣኔ ሀብት፣ በደን ምርት ግብይትና ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረ ምርምር በማካሄድ ቴክኖሎጂዎችን፣ መረጃዎችንና እውቀቶችን ማውጣት፣ ማላመድ፣ ማስተዋወቅ፣ ማሰራጨትና እንዲሰርፅ ማድረግ፣ ማማከር ነው፣

8/ **"Forestry Research"** means conducting scientific studies in the areas of establishing forests and agroforestry systems and managing and using them, wood industries, forest ecosystems and climate change, value addition on forest products, on policy and socio-economic aspects, on marketing of tree and forest products and services and generating, popularizing, and disseminating information, knowledge, and technologies to accelerate the development of the forestry sector;

፱/ **"የተጎሳቆለ መሬት"** ማለት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቱ የቀነሰና ምርታማነቱን ያጣ እና የማገገም ስራዎች የሚሰሩበት መሬት ነው፣

9/ **"Degraded Landscape"** means land that has lost productivity and its ecological services have significantly declined and hence requiring rehabilitation;

፲/ **"ሥነ-ሕይወታዊ መንገድ"** ማለት የተጎሳቆለን መሬት ሥነ-ሕይወታዊ መንገድን በተለይም ዕፅዋትን በመጠቀም እንዲያገግም የማድረግ ዘዴ ነው፣

10/ **"Biological Means"** refers to ways of assisting restoration of degraded land using biological means, notably plants;

፲፩/ **"ዕፅዋት"** ማለት ከሰብል ዝርያዎች በስተቀር ዕድሜና መጠን ሳይለይ ማንኛውንም ተክል የሚያጠቃልል ነው፣

11/ **"Plant"** refers to all types of plants that are not commonly considered as crops, irrespective of age or height;

፲፪/ **"አነስተኛ ደን"** ማለት እስከ አምስት ሄክታር በሆነ መሬት ላይ የሚለማ፣ የሚጠበቅና ጥቅም ላይ የሚዉል ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ ደን ነው፣

12/ **"Small Scale Forest"** means planted or natural forest developed, protected and utilized on a maximum of five hectare of land;

፲፫/ **"ሰፊ ደን"** ማለት በግል፣ በማህበር ወይም በመንግሥት ከአምስት ሄክታር በላይ በሆነ በአንድ ቦታ ወይም በኩታ ገጠም የሚለማና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን የደን ዉጤት የሚመረትበት ወይም ለሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት የሚጠበቅ ደን ማለት ነው፤

፲፬/ **"ማዕከል"** ማለት የደን ልማት፣ ምርምርና ስልጠና ሥራዎች የሚተገበርበት የኢትዮጵያ ደን ልማት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ነው፤

፲፭/ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ የተዘረዘሩት ትርጓሜዎች በዚህ ደንብም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፤

፲፮/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፯/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

፲፰/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፱/ በወንድ ጾታ የተገለፀው ማንኛውም አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሌሎች ቦታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

13/ **"Large Forest"** means forest protected or planted and managed either privately, by associations or the government on single plot of land or a cluster arrangement to produce forest products and supply inputs to industries or for provisioning ecosystem services;

14/ **"Center"** means a branch office of Ethiopian Forestry Development that conducts forestry development, research and training activities;

15/ The definitions provided in the Forest Development, Protection and Use Proclamation No. 1065/201 shall apply to this Regulation;

16/ **"Region"** means any State referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

17/ **"Minister"** means the Minister of Agriculture;

18/ **"Person"** means any natural or juridical person;

19/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Head Office

Ethiopian Forestry Development shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere.

## ፬. ሥልጣንና ተግባራት

የኢትዮጵያ የደን ልማት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የደን ሀብታችንን በዘላቂነት ለማልማት፣ ለመጠበቅና በአግባቡ ለመጠቀም፣ ምርምርንና ስልጠናን ለማሳለጥ የሚያስችሉ የፖሊሲና የስትራቴጂ ረቂቅ ሃሳብ እና የሕግ ማዕቀፎችን በማቅረብ እንዲጸድቅ ክትትል ያደርጋል፤ ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ ከክልሎች ጋር በመተባበር ደንና የደን መሬት እንዲለይ፣ እንዲከለል፣ እንዲመዘገብ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖረው፣ ደኖች ምርት ሰጭ ደንና ጥብቅ ደን ተብለው እንዲለዩ እና የደን አያያዝና አስተዳደር ዕቅድ እንዲኖራቸውና በዘላቂነት እንዲለሙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ ይደግፋል፡፡

፫/ ፍጹም ጥብቅ ደኖች ተለይተው በዘላቂነት እንዲጠበቁ ተቋሙ የሕግ ረቂቅ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሕጉ ሲጸድቅም ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፬/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገራችንን የደን ሀብት ሽፋን ሁኔታና ለውጥ፣ የደን አይነትና እድገት፣ የካርቦን ክምችት፣ የደን ኢንዱስትሪና የደን ውጤቶች ምርትና ፍላጎት፣ የገቢና ወጭ ንግድ መረጃ እንዲሰበሰብና የደን ዘርፍ ለምጣኔ ሀብት እና ማህበራዊ እድገት እንዲሁም ለሥርዓተ-ምህዳራዊ አገልግሎት ያለው አስተዋጽዖ

## 4. Power and Duties

Ethiopian Forestry Development shall have the following power and duties:

1/ Formulate, submit and follow up the review and approval of policies, strategies, and legal frameworks to facilitate the conservation, development and sustainable use of forests, to expedite research and trainings, and implement same when approved.

2/ Collaborate with relevant Regional authorities, identify, demarcate, register, and secure land use right certificates for forests and forestlands; classify forests into protection and production forests on their intended uses and make sure that all forests have management plans and are managed accordingly in collaboration with relevant stakeholders.

3/ Identify reserve forests and prepare draft law and submit to the Ministry to legally designate and fully protect them, and when approved, work with relevant authorities to implement the law.

4/ Gather, synthesize, and compile information on the changes in forest types, cover, and health; on forest carbon stock; on forest industries; on the supply and demand as well as on import and export data of forest products; on the contribution of the forestry sector to the socio-economic

እንዲተነተን፣ እንዲሰራጭና ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይደግፋል፡፡

፭/ ዘላቂ የደን ልማት፤ ጥበቃና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፓኬጆችን ያዘጋጃል፤ በማዕከላቱና በሌሎች አመቺ አደረጃጀቶች በመታገዝ የስርፀት ሥርዓትና አገልግሎት የሚሰጥበትን አሠራር ይዘረጋል፤ ይደግፋል፡፡

፮/ ዘላቂ የደን ልማት ሥራዎችን ለማከናወንና ለመደገፍ ከሚመለከታቸው የመንግስትና ልማት አጋር አካላት ጋር በመተባበር ተጨማሪ ሀብት ያሰባስባል፤ የደን ፈንድ እንዲቋቋምና ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ይሰራል፤ የደን አልሚዎች የቢዝነስ ዕቅድ እንዲኖራቸው፣ የብድርና የኢንሹራንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፡፡

፯/ ያሉትን የልማትና የምርምር መሬቶች፣ የሙከራ ጣቢያዎች፣ የዘር ማመንጫ ቦታዎች፤ የችግኝ ጣቢያዎች፣ ቤተ-ሙከራዎች፣ ማዕከላት፣ ንዑስ ማዕከላትንና ሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ይዘጋል ወይም በሚኒስቴሩ ሲፈቀድ አዳዲስ ይከፍታል፡፡

development; and ecosystem services; and ensure the dissemination and wider use of information.

5/ Prepare extension packages and through its centers and other paths to facilitate sustainable forest development conservation and use by putting in place and supporting efficient extension system and extension service accessible to users.

6/ Mobilize additional resources for sustainable forest development by working with government institutions, development partners; closely work to advance the establishment of forest fund, and operationalize it when approved; and work with, provide support and follow up with relevant institutions to ensure that forest developers have business plan, access to finance and insurance services.

7/ Run and expand existing research centers, sub-center, research fields, lands, seed stands, nurseries, laboratories, and other infrastructure, and close existing ones and to acquire or establish new ones when approved by the Ministry.

፰/ አነስተኛና ሰፋፊ ሰው ሠራሽ ደኖች እንዲለሙ፣ የተፈጥሮ ደኖች በዘላቂነት እንዲጠበቁ፣ የተራቆቱ ደኖችና መሬቶች እንዲያገግሙ በክልሎች ዕቅድና የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሲቀርብ ከመንግሥትና ከልማት አጋራት በማመደብ በጀት ስራውን ይመራል፣ ይደግፋል፡፡

8/ Utilize budget secured from the Government and development partners to lead and support the expansion of small- and large-scale plantation forests, protection of natural forests, and rehabilitation of degraded forests and landscapes when Regions present such request as part of their Regional plan and with land use right certificate indicating the land where such intervention is to be implemented is properly demarcated and legally certified.

፱/ ከሚመለከታቸው ተቋማትና አጋር አካላት ጋር በመተባበር የተራቆቱ መሬቶች በዛፍና ሌሎች ዕፅዋት ተሸፍነው እንዲያገግሙና በኩታ ገጠም ዘዴ እንዲለሙ በማድረግ የውሃ አካላት እና ሌሎች ለጎርፍና መሬት መንሸራተት ተጋላጭ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮችና አካባቢዎች እንዲጠበቁ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይሠራል፡፡

9/ Closely work with concerned stakeholders in undertaking restoration of degraded landscapes using trees and other vegetation, promote cluster based tree planting and landscape rehabilitation, and rehabilitate areas around water bodies, around infrastructure, and landscapes susceptible to flooding and landslides.

፲/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የከተማ ደንና አረንጓዴ ቦታዎች እንዲስፋፉ እና በዘላቂነት እንዲለሙ በማድረግ የደን ዘርፍ በከተማ ወስጥና ዙሪያ የሚኖረውን የሥራ ፈጠራና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሥርዓተ-ምህዳራዊ ፋይዳዎች እንዲጎለብቱ ያደርጋል፣ ይደግፋል፡፡

10/ In collaboration with concerned institutions, promote urban forestry and support the expansion of urban green spaces and the sustainable development of urban and peri urban forests in ways that enhance their contributions for job creation and for other economic, social, and environmental benefits.

፲፩/ ጥራቱን የጠበቀ የዛፍና ሌሎች ዕፅዋት ዘር ማመንጫዎች እንዲቋቋሙ፣ እንዲጠበቁ፣ ዘር በአግባቡ እንዲሰበሰብ፣ እንዲፈተሽ፣ እንዲከማች፣ ደረጃ እንዲወጣ፣ የጥራት ማረጋገጫ ሰነድ እንዲኖርና ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ያደርጋል፤ የአሠራር ሥርዓትና መሠረተ ልማት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ይደግፋል፡፡

፲፪/ ነባር ችግኝ ጣቢዎች እንዲጠናከሩና እንዲዘምኑ፣ አስፈላጊ ሲሆን አዳዲስ ችግኝ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ፣ ካርታና የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲኖራቸው፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች እንዲፈሉ፣ ለተፈለገው አገልግሎት በተስማሚ ቦታ እንዲተከሉና ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ይደግፋል።

፲፫/ የአረንጓዴ አሻራ የማህበረሰባችን እሴት ሆኖ እንዲሰርጽ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ህዝባዊ የዛፍ ተከላ ቀን እንዲኖር ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስወስናል፤ ተግባራዊነቱን ያስተባብራል፡፡

11/ Establish and maintain seed sources to produce quality tree seeds and other planting materials to ensure that seeds are collected, tested, and stored appropriately to set quality standards and to ensure that seeds meet these standards, have certificates, and distributed to users timely and ensure that the required infrastructure to do so is built and the legal and institutional framework to enforce same is put in place and laws enforced.

12/ Expand and modernize existing nurseries and establish new ones to ensure that all nurseries have land use right certificates to support them to produce more and quality seedlings that meet the standards to ensure that these seedlings are planted at the right time, at the right place and for the desired objectives, and that the seedlings receive the care needed to meet planting objectives.

13/ Work to increase awareness among citizens so that the spirit of the Green Legacy Initiative becomes societal asset, and propose to the government a designation of a national tree planting date, and implement same when approved.

፲፬/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለደን ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ የደን አያያዝ፣ አስተዳደር፣ አጠቃቀምና የደን ምርቶችና አገልግሎቶች ደረጃ እንዲወጣ፣ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ እና ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፤ ይደግፋል።

፲፭/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የደን ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂዎች፣ ማሽነሪዎችና ግብአቶች እና ከሀገር የሚወጡ የደን ምርት ዓይነቶችን ደረጃ እንዲወጣ ይሠራል፤ ይደግፋል፡፡

፲፮/ የደን ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋና የገበያ ትስስር እንዲጠናከርና የሥራ ዕድል እንዲፈጠር፣ ከዉጭ የሚገቡ የደን ዉጤቶች በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተኩና የደን ዉጤቶችን ወደ ውጭ በመላክ የዉጭ ምንዛሬ እንዲገኝ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይሠራል፡፡

፲፯/ የተፈጥሮ ደኖችን በመንከባከብ፣ እንዲያገግሙና በዘላቂነት እንዲጠበቁ በማድረግ የአየር ንብረት ለዉጥ በሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች፣ በሰውና መሠረተ-ልማቶች ላይ የሚያስከትላቸዉን ጎጂ ተጽዕኖዎች ለመከላከልና ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ ይልቁንም የደን ዘርፍ ለበካይ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ሚናው የጎላ እንዲሆን ይሠራል፤ ይደግፋል፡፡

14/ Collaborate with relevant authorities and establish standards for inputs used in forestry for forest establishment, management, and use; and for forest products and services; and put in place marketing systems; and ensure that the standards and systems are operationalized, and laws are enforced.

15/ Establish standards for forest industry technologies, machineries and other inputs or products to be imported and for forest products to be exported and collaborate with concerned authorities to enforce them.

16/ Support efforts to expand forest industries and create market links for forest products in view of creating jobs, substituting wood product imports with products produced in the country, and increasing foreign currency earnings by promoting export of forest products.

17/ Ensure the protection, rehabilitation, sustainable management and use of natural forests to significantly contribute to climate change mitigation and minimize the negative impacts of climate change and variability on ecosystem services, on people and on infrastructure.

፲፰/ የደን ጭፍጨፋና መራቆትን ለመከላከል፣ እየተስፋፋ የመጣውን መጤና ተዛማች አረሞች፣ የደን በሽታ፣ ነፍሳት-ተባይና የደን እሳት መንስዔዎችን ይለያል፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሰው ኃይል፣ የሎጂስቲክስና የመሠረተ ልማት አቅም ይገነባል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፡፡

፲፱/ በደን ላይ የሚደርሱ ጥፋቶችና በደን ምርት ዝውውር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር ይከላከላል፣ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፳/ የደን ዘርፍ ልማት፣ አስተዳደር፣ አጠባበቅና አጠቃቀም ማህበረሰብ አሳታፊና አካታች እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይሰራል፣ ይደግፋል፣ እንዲሁም ከደን ልማት የሚገኝን የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የማህበረሰብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፡፡

18/ Build the human, logistical, and infrastructural capacity of the Ethiopian Forestry Development to identify and address causes and effectively combat deforestation and forest degradation, forest fire, forest pests and diseases, and invasive species, and to coordinate and lead such efforts at all levels.

19/ In collaboration with relevant Federal and Regional Authorities, support the prevention and control of crimes on forests and combat illegal forest products trade and ensure that administrative and legal measures are taken on wrong doers.

20/ Ensure that the forestry development contributes to economic development in ways that is participatory, socially, and regionally inclusive, and put in place and operationalize mechanism that ensures equitable benefits to communities from sustaining ecosystem service provisions.

፳፩/ በደን እና ጥምር ደን ግብርና ልማት፣ አያያዝ፣ ጥበቃና አጠቃቀም፣ በደን ሥርዓተ-ምህዳር፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በደን ምርት እሴት መጨመር፣ በፖሊሲና ምጣኔ ሀብት፣ በደን ምርት ግብይትና ኢንድስትሪ ምርምር በማካሄድ ቴክኖሎጂዎችን፣ መረጃዎችንና እውቀቶችን ያወጣል፣ ያሰራጫል፣ ያስተዋውቃል፡፡

21/ Conduct research on agroforestry and forest development; on forest conservation, management, and use; on forests and ecosystem services; on climate change and forests; on forest policy and governance; on forests and their socioeconomic contributions; on value addition and marketing of forest products and services; and on forest industries and to generate evidence, knowledge, and technologies for forest sector development and to facilitate wider use of same.

፳፪/ የአካባቢ መጎሳቆል፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣ እንዲሁም የደን ዝርያዎችን መጥፋት ለመቀነስና የደን ውጤቶች አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ የዱር ሙጫና ቀርከሃን ጨምሮ ሌሎች ፈጣን እድገት ያላቸውን የዛፍ ዝርያዎች ያላምዳል፣ ያሰራጫል፡፡

22/ Identify, adapt and promote gums and resins bearing species, bamboo, and other fast growing tree species to combat environmental degradation, desertification and loss of forests and biodiversity and to significantly increase the supply of forest products.

፳፫/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አነስተኛና ሰፋፊ እርሻዎች፣ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ባሉባቸውና በሚስፋፋባቸው ቦታዎች በምርምርና ቴክኖሎጂ ተደግፎ በሕግ የተደነገገ የዛፍ ብዛት እንዲኖር ይሠራል፣ ይደግፋል፡፡

23/ Collaborate with relevant authorities to ensure the presence of legally sanctioned number of trees through research and technology on small and large scale farms and where there are irrigation infrastructures.

፳፬/ ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የተገኙ የደን ምርምር ውጤቶችን በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

24/ Ensure that forestry innovations from domestic and international sources having proven records are compiled and made accessible to users.

፳፭/ ከምርምር ሥርዓቱ ለሚወጡና የላቀ ሀገራዊ ፋይዳ ላላቸው ቴክኖሎጂዎችና ዕውቀቶች የአዕምሯዊ ንብረት መብት እውቅናና ጥበቃ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፳፮/ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉራዊና በቀጣናዊ የበረሃማነት መከላከል፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በአየር ንብረት ለውጥ መከላከል፣ በተባበሩት መንግስታት የደን ካርቦን ልቀት ቅነሳ፣ በዓለም አቀፍ የደን ፎረም፣ በአፍሪካ ታላቁ አረንጓዴ ግንብ፣ በዓለም የቀርከሃ እና ሸመል ኔትወርክ፣ በአፍሪካ የተጎዱ መሬቶች መልሶ ማገገም ፕሮግራምና በሌሎች ተያያዥ የደን ዘርፍ መድረኮች ላይ ይወከላል፣ ይሳተፋል፣ የኢትዮጵያ ጥቅም መከበሩን ያረጋግጣል፡፡

፳፯/ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ ከሚሰሩ የኢንዱስትሪ፣ የትምህርት፣ የምርምርና ሥልጠና ተቋማት እና የአምራችና የሙያ ማህበራት፣ ከግል ዘርፍ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

25/ Work with appropriate agencies to legally protect intellectual property rights for research outputs and technologies generated by the Ethiopian Forestry Development.

26/ Represent the forestry sector and participate in international, continental, and Regional platforms, notably United Nation Framework Convention on Climate Change (UNFCCC), United Nation Convention to Combat Desertification (UNCCD), United Nation Forum on Forests (UNFSS), United Nation Reducing Emission from Deforestation and Forest Degradation (UN REDD+), African Great Green Wall, International Bamboo and Rattan Organization (INBAR), African Forest Landscape Restoration (AFR 100), and other forestry related forums and to advance national interests in these platforms.

27/ Collaborate with industries, research, educational and training institutions, as well as with producer and professional associations, the private sector, and non-state actors in the country engaged in forestry development.

፳፰/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፣ የደን ምርቶች ማምረትና ማዘዋወር ፈቃድ፣ የላቦራቶሪ አገልግሎት፣ የእፅዋት ዘር አቅርቦት እና ሌሎች አገልግሎቶች ይሰጣል፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

፳፱/ በስሙ ንብረት ያፈራል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

፴/ በዚህ ደንብ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ የተጠቀሱትን ሥልጣንና ተግባራት ይተገብራል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

## ፭. አደረጃጀት

የኢትዮጵያ ደን ልማት፡-

፩/ ዋና ዳይሬክተር

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

## ፮. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ልማቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

28/ Issue certificates of qualification in forestry, permits for harvesting and transportation of forest products, and provide laboratory services; plant seed supply, and other services and collect payments for the provided services based on Regulation to be issued by the council of ministers.

29/ Own property, enter in to contract, sue and be sued in its own name.

30/ Undertake all other tasks necessary to execute its power and duties stated under this Regulation, and in the Forest Development, Conservation, and Use Proclamation No. 1065/2018.

## 5. Organization

The Ethiopian Forestry Development shall have:

1/ A General Director

2/ Deputy General Directors as required; and

3/ Necessary employees;

## 6. Power and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the Chief Executive Officer of the Development and shall direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of the Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

ሀ) የኢትዮጵያ ደን ልማትን ዓላማ ለማሳካት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተደነገጉትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግና መሠረታዊ መርሆን ተከትሎ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሐ) አመታዊ የሥራ በጀትና እቅድ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ያስጸድቃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ) የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

ሠ) ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የኢትዮጵያ ደን ልማትን ይወክላል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለልማቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፯. የምክትል ዋና ዳይሬክተር ስልጣን እና ተግባር

፩/ የተመደበበትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተዉ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሰራል፣ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ካሉ እና ዋና ዳይሬክተሩ በግልፅ ካልወከለ በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል፡፡

a) exercise the power and duties of the development specified under Article 4 of this Regulation;

b) employ, administer and terminate employees in accordance with the Federal Civil Service Law and Principles;

c) prepare and submit annual plans and budget to the Ministry and implement the same upon approval;

d) prepare and submit the performance and financial reports to the Ministry;

e) represent the development in its dealing with third parties.

3/ The Director General may delegate part of his power and duties to other heads and staff for better and efficient performance of activities in the development.

## 7. Power and Duties of the Deputy General Director

1/ Lead and administer the department assigned to them.

2/ Perform tasks assigned by the Director General.

3/ Unless the Director General delegates otherwise, the senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence.

**፰. <u>በጀት</u>**

የኢትዮጵያ ደን ልማት በጀት በመንግሥት ይመደብለታል።

**፱. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

የኢትዮጵያ ደን ልማት፦

፩/ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**8. <u>Budget</u>**

The Budget of the Ethiopian Forestry Development shall be allocated by the Government.

**9. <u>Books of Accounts</u>**

The Ethiopian Forestry Development shall keep:

1/ Complete and accurate books of accounts;

2/ The book of accounts and financial documents of the Ethiopian Forestry Development shall be audited annually by Auditor General or an auditor assigned by Auditor General.

## ፲. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መያዚያ ፮ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 10. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 14th Day of April, 2022**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**